የአውሮፓና የአፍሪካ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ምክር ቤት
The Council of European and African Kinijit Support Groups

1 Crowndale Road London NW1 1TU UK Tel: +44 (0) 20 7168 9893 Email: euafkinijit@googlemail.com

# <u>በመላው አውሮፓ ለምትገኙ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ፣</u>

በፊታችን ዲሰምበር 7 እስከ ዲሰምበር 9/2007 በፖርቱጋል ዋና ከተማ ሊዝቦን ውስጥ ሁለተኛው የአውሮፓና የአፍሪካ መሪዎች የጋራ ስብሰባ የካሄዳል:: በዚህ ስብሰባ ላይ የአምባገነኑ ወያኔ/ኢህአዴግ ተጠሪ አቶ መለስ ዜናዊ እንደሚሳተፍ ከቅርብ ምንጮቻችን ለማወቅ ተችሏል::

በዚህ ስብሰባ ላይ መሪዎቹ ከሚነጋገሩባቸው ጉዳዮች መሀከል፣ሰላምና ድህነት፣ዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት፣የዜጎች ከሀገር ሀገር መሰደድና የአየር ንብረት ለውጥ ይገኙባቸዋል::

ወያኔ፣ የአፈና አገዛዝ መረቡን በተለይ ከምርጫ 97 ወዲህ፣ ከዳር እስከዳር በመዘርጋት፣ ሐገሪቱን ወደ አንድ ትልቅ እስር ቤት ቀይሯታል:: ከዛሬ ሁለት አመት በፊት የተሰረቀ ድምጻቸውን ለመጠየቅ በተሰለፉ 193 ንጹህ ዜጎች ላይ በአደባባይ ያደረሰውን የጭፍጨፋ አረመኔያዊ እርምጃ አልበቃ ብሎ፣;

- አሁንም ኢትዮጵያ ዜጎቿ፣ ለሞት፣ለእስር፣ለስደት ይዳረጋሉ::
- አሁንም ኢትዮጵያ ዜጎቿ፣ በተሰደዱበት የበአድ ሐገር ይታደናሉ::
- አሁንም ኢትዮጵያ ልጆቿ፣ በአለኮሱት የጦርነት እሳት ይጋየሉ::

የዚህ ዘረኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ቁንጮ አቶ መለስ ዜናዊ፣የሰው ልጆች ድምጻቸውን በነፃነት በሚያሰሙባት የአውሮፓ ምድር፣ ያለምንም ተቃውሞ ስለ ዲሞክራሲ እንዲመጻደቅ መፍቀድ፣ ለነፃነት ሲሉ የወደቁትን አርበኞች አደራ ከመብላት ይቆጠራል::

በመሆኑም በአለፈው አመት በብረስልስ በተደረገው ተመሳሳይ ስብሰባ ላይ ይህንን የቀበሮ ባህታዊ አሳፍረን እንደመለስነው ሁሉ፣አሁንም የዚህን ፋሽስታዊ አገዛዝ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ለስብሰባው ተሳታፊዎችና ለውቅቱ የአውሮፓ ፕሬዝዳንትነቱን ለያዘው ለፖርቱጋል መንግስትና ሕዝብ ለማጋለጥ ወገናዊ ጥሪ ቀርቧል::

ሰላማዊ ሰልፉ የሚደረገው ቅዳሜ ዲሰምበር 8 /2007 ከጠዋቱ ሦስት ሰአት ጀምሮ ሲሆን፣ የወገናችሁ ጉዳይ የሚያንገበግባችሁ ወገኖች ሁሉ፣ ከተለያዩ የአውሮፓ ሐገሮች እንደምትመጡ ይጠበቃል::

የሰልፉ ቦታ: ከስብሰባ አዳረሹ ፊት ለፊት ሲሆን፣ ከዚህ በታች ያለውን ሊንክ ይጫኑ፣

http://www.eu2007.pt/UE/vEN/Reunioes_Eventos/ChefesEstado/EUAfrica.htm

ለበለጠ መረጃ የኢሜል አድራሻችን: euafkinijit@googlemail.com
kinijitsup@yahoo.com

## የአውሮፓና የአፍሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ምክር ቤት፣